# የማይሞቱ ቃላት ፤

ትጉሃን መላእክት ለተልዕኮ እንደሚፋጠኑ የሰው ዘርም በጊዜ ወፍቅነትና በሥራ ክቡርነት አምኖ እንዲ ተጋ ትንሣኤ ልቡና ሊኖረው ይገባል ፤—

—«ለመሥራት የማይወድ ቢኖር አይብላ !»

ቅዱስ ጳውሎስ (፪ ተሰ ፥ ፫ ፥ ፲) ።



—«ጊዜ እየበረረ ሳይታጠፍ ክንፉ
እኛ በቁማችን ምንድንነው ዕንቅልፉ ?
ካልተሣፈሩበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ
ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ ፡
ከጊዜ ጋር አብረው ለሚገሠግሡ
ዕንቅፋት የለውም ባሕሩም ሆነ የብሱ » ።

አበባው ይግዛው

«በዘመን ግሥጋሤ ዕድሜያችን ተማርኮ
ያለፍነው እኛ ነን ጊዜ አይደለም እኮ » ።

ከበደ ሚካኤል

በኢት፣ ኦ/ ተ/ ቤ/ ክ/ ስብከተ ወንጌልና
ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ታተመ ።

ዋጋው ብር 1.00

# መልአከ ብሥራት



« አነ ገብርኤል ዘእቀውም
ቅድመ እግዚአብሔር »

ት/ ዘ/ ማ/ ቤት ።

www.ethiopianorthodox.org

# መልእከ ብሥራት

« እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆም ገብርኤል ነኝ» ሉቃ ፩ ፲፱

አዘጋጅ

መጋቤ አዕላፍ መክብብ አጥናው

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ

ገጽ


፩ መግቢያ . . . . . ፫

፪ የመላእክት ሥነ ተፈጥሮና አገልግሎት . . ፬

፫ ንቁም በበህላዌነ . . . . ፯

፬ ሀብተ ብሥራት . . . . . . ፲፩

፭ ሕፃኑ ሰማዕትና የተላከለት ታዳጊ መልአክ . . ፲፰


# መግቢያ ።

የዚህ አጭር ጽሑፍ ዝግጅት ዋና ዓላማ ቅዱሳ
መላእክት የተገኙበትን ረቂቅ ሥነ ተፈጥሮና አገልግ
ታቸውንም መግለጥ ነው ።

ስለዚህም ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ትእዛዝ በ
ጊዜው አማኞችን በመርዳትና ታማኞች ምስክሮችን(ሰ
ዕታትን) ከእሳት ከስለትና ከማናቸውም አደጋ በመታደ
ተግባር ምን ያህል እንደሚተጉና በነርሱ ያደረ የእግዚ
ብሔር ኃይልና ድንቅ ሥራው እንዴት እንደሚከሠ
በመተንተን መነሻ የሚሆን ፍሬ ሐሳብ በማቅረብ ሬገ
በወንጌል ሰባክያን መምህራንና የትምህርቱ ተቀባዮ
በሆኑት ምእመናን፤መካከል የሐሳብ መገናኛ ድልድይ እ
ደሚሆን ይታመናል ።

ዝግጅቱም በዚህ ብቻ የሚገታ ሳይሆን በተለይ በ
ገራችንና ከሀገር ውጭም ጭምር በስማቸው አብያተ ክር
ቲያናት የታነጹላቸውንና ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው
ኃይል መሠረት ገቢረ ታምራት በማድረግ የታወቁት
የዋና ዋናዎቹን ሊቃነ መላእክት የትድግና ተልእኮ የሚ
ገልጥ እትም በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶአል ። ቸርነ
የማያልቅበት አምላክ ለፍጻሜው እንዲረዳን እንለምነ
ለን ።

መ/አዕ- መክብብ አጥናው

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ፩ ።

## የመላዕክት ሥነ ተፈጥሮና አገልግሎት

ቅዱሳን መላእክት ከምን ስለምን አገልግሎት እንደ ተፈጠሩ ዳዊት ሲገልጥ በአንድ ዐረፍተ ነገር በማጣመር አጠቃሎት ይገኛል።ይኸውም «ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት መላእክቱን ነፋሳት አገልጋዮቹንም ነደ እሳት የሚአደርጋቸው እርሱ ነው» ሲል የተናገረው ቃለ መዝሙር ነው ።

ይህም ጣምራ አገላለጥ በአጭር የትርጉም ትንታኔ ሲታይ ፡ የመላእክት ተፈጥሮ ከነፋስና ከእሳት ነው ወይም እምኀበ አልቦ ነው የሚሉ አሉ ።

እሳት ነፋስ ኃያላን ረቂቃን ፈጣኖችና ፈጻምያነ ፈቃድ እንደሆኑ መላእክትም በተግባራዊ ተልእኮዋቸው ይህ ዓይነቱ ጠባይ አላቸው ።

፩/ አገልግሎታቸውም ከስማቸው የተባበረ ነው። ይኸውም «መልአክ» የሚለው ስም በግዕዝም ሆነ በዕብራይስጥ ቃል በቃል የሚሰጠው ትርጉም የሚላክ ወይም ተፈናዊ፣ ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ከሰው ወደ እግዚአብሔር በመላላክ አገልግሎቱን የሚፈጽም ማለት ነው ።



## ማኅሌታዊ አገልግሎት

፫/ ሌላው የመላእክት አገልግሎት እጅግ ጣፋ በሆነ ጣዕመ ዜማ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው«አንዱ ከሌላው ጋር በመቀባበል ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ የሠ ዊት ጌታ የሆንህ እግዚአብሔር ሆይ! ምስጋናህ ምድ ሁሉ ሞላ ፡ እያለ በታላቅ ድምፅ በመጮህ ያመሰግን ነበ ከድምጹም ታላቅነት የተነሣ የቤቱ መቃን ፡ መድ ቁጭ ብድግ ማለት ጀመረ» ይላል (ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩—

ሔኖክ በትንቢቱ፣ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድም በ እዩ፣ዳዊት በመዝሙሩ (ወዘተ - - ) እንደ ገለጡት መ ክት ለፈጣሪያቸው የሚያቀርቡት ውዳሴና ቅዳሴ ሌሊ ከቀን የማይገታ ነው (ራእ ፡ ፬ ፡ ፰—፱)

አባ ሕርያቆስም የመላእክቱን ማኅሌታዊ የምስ ጣዕም ሲገልጥ «ዘያጠልል አዕዕሞተ እምብዝኀ ጣዕ ፈቡፋደ ከጣዕሙ ብዛት የተነሣ አጥንትን የሚ መልም ነው» ብሏል ።



www.ethiopianorthodox.org

## አስተርእዮተ መላእክት

## የመላእክት መገለጥ

፪/ በዓይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ የግዙፍ አካል ባሕርይ የሌላቸውና በተፈጥሮዋቸው ረቂቃን መናፍስት የሆኑ ቅዱሳን መላእክት ለምሕረትም ሆነ ለመዓት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው በሚላኩበት ጊዜ በሰብአዊ መልክና አካል ተገልጠው እንዲታዩ እና በሰብአ ዓለም ቋንቋ እንዲናገሩ የአምላክ ፈቃድ ሆኗል ።

ስለዚህም እንደ ቃለ ዓዊ ከእግዚአብሔር የተላኩ ሐገልጋዮች መሆናቸውን አስታውቀው ፥ ልዩ ልዩ ተልእኮ መፈጸማቸው ጥንት በአበው ዘመን የተለመደና አሁንም በመደገም ላይ የሚገኝ መሆኑ በተግባር እየታየ ነው።



## ክፍል ፪

## ንቁም በበህላዌነ እስከንረክቦ ለፈጣሪነ

« ፈጣሪያችንን እስክናገኘው ድረስ በየአለንበት ፀንተን እንቁም» ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል የተናገረው ቃል ነው ። ይህም የተነገረበት ምክንያት በቅዱሳን መላእክት ጥንተ ፍጥረት የመላእክት ሁሉ አለቃ ቅሩብ እግዚአብሔር ፥ አኀዜ መንጦላዕት ይሆን ዘንድ ልዕልና ተሰጥቶት የነበረው ሳጥናኤል የማዕርጉን ታላቅነት በመመልከት ታብዮ ፈጣሪውን ከመካዱ የተነሣ በማኅበረ መላእክት መሀከል የነበረውን ሁከት ለማረጋጋትና ጸጥ ለማድረግ እንደ ነበር ተጽፎአል ።

በመሠረቱ ሊቀ መላእክት ቅ/ገብርኤል መጋቤ ሐዲስ ተብሎ ይጠራል ። ይህን በምንልበት ጊዜ ግን በዘመነ ብሉይ የሥራ ድርሻ ያልነበረው ማለት አይደለም ። መጋቤ ሐዲስ መሆኑ በይበልጥ ጐልቶ የታየበት ምክንያት «ይህን ዓለም ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል» ተብሎ የተነገረለት አምላክ ሰው የሚሆንበትን ከድንግል የሚወለድበትን ምሥጢር ለአምላክ እናት ለማብሠር የተላከ ዜናዌ ሐዲስ በመሆኑ ብቻ ነው እንጂ በዘመነ ብሉይም የሥራ ድርሻ እንደ ነበረውማ ስሙ ከነግብሩ የተገለጠበት ክፍል አለ ። ለማስ



www.ethiopianorthodox.org

ረጃም ያህል በትንቢተ ዳንኤል ምዕ ፡ ፰ ፡ ፲፭—፳ የተጻፈውን ብንመረምር ይህ መልአክ በዘመነ ብሉይም ቢሆን መጋቢ ራእይ ወትንቢት እንደ ነበረ እንረዳዋለን ። ለዚህም ጥቂት ነጥቦችን እንጥቀስ ።

፩/ በቍጥር ፲፭—፲፮ «እኔም ዳንኤል ራእዩን ባየሁ ጊዜ ትርጕሙን ማስተዋል ፈለግሁ እነሆም ሰው የሚመስል በፊቴ ቆሞ ነበር ፡— በኡባልም ወንዝ መካከል» «ገብርኤል ሆይ የዚህን ራእይ ትርጉም ለዚህ ሰው አስታውቀው ብሎ በመጮህ የሚናገረውን ሰው ድምፅ ሰማሁ ።

፪/ በቁጥር ፲፯ እርሱም «የሰው ልጅ ሆይ ራእዩ ለፍጻሜ ዘመን የተዘጋጀ መሆኑን አስተውል አለኝ» ካለ በኋላ የራእዩን ትርጕም እንዴት አድርጎ በመተንተን እንዳስረዳው መመልከት ይቻላል ።

ይኽን ምሥጢር ለቅዱሳኑ የገለጠ አምላክ ስሙ ይመስገን ።

«አኮኑ ኵሎሙ መላእክት መንፈስ እሙንቱ ወይትፌነው ለመልእክት በእንተ እለ ሀለዎሙ ይረሡ ሕይወተ ዘለዓለም፡መላእክትማ የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሱ ዘንድ የተመረጡ ሰዎችን ለመርዳትና ለማገልገል የሚላኩ ረቂቃን መናፍስት ናቸው» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ዕብ ፡ ፩፡ ፲፬) በሃይማኖት ጽናት ለእውነተኛ ምስክርነት የሚቆሙ ሰማዕታትን ለመርዳት እግዚአብሔር አምላክ በየጊዜው ከሚልካቸው መንፈሳውያንና አሳታውያን መላእክት አንዱ ሊቀ መላእክት ቅ/ገብርኤል ነው ።

በየዐረፍተ ዘመኑ ፍጡነ ረድኤት ሆኖ በፈጸመውም ተልዕኮ ሁሉ በተለይ እንደ አጥቢያ ኮከብ የሚያበራ ታሪክ ያለው ድንቅ ሥራው ሠለስቱ ደቂቅን ከነደደ እሳት መታደጉ ነው ። ይኸውም ታሪክ በትንቢተ ዳንኤል ምዕ፡፫ እንደሚከተለው በሰፊው ተገልጿ ።



«ንጉሡ ናቡከደነፆር ቁመቱ ስድሳ ክንድ ወርዱም ስድስት ክንድ የሆነውን የወርቁን ምስል አሠራ ፤ በባቢሎንም አውራጃ በዱራ ሜዳ አቆመው ። ንጉሡም ናቡከደነፆር መኳንንትንና ሹማምንቶችን ፡ አዛገሮችንና አዛውንቶችን ፡ በጅሮንዶችንና አማካሪዎችን ፡ መጋቢዎችንም ፡ አውራጃ ገገሮችንም ሁሉ ይሰበሰቡ ዘንድ ፡ ንጉሡም ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል ምረቃ ይመጡ ዘንድ ላከ ፡ በዚያን ጊዜም መኳንንቱና ሹማምቶቹ ፡ አዛገሮቹና አዛውንቶቹ ፡ በጅሮንዶቹና አማካሪዎቹ ፡ መጋቢዎቹና አውራጃ ገገሮቹ ሁሉ ንጉሡ ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል ምረቃ ተሰበሰቡ ፤ ናቡከደነፆርም ባቆመው ምስል ፊት ቆሙ ። አዋጅ ነጋሪውም እየጮኸ እንዲህ አለ፡— ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የምትናገሩ ሆይ ፡የመለከትንና የእንቢልታን ፡ የመሰንቆንና የክራርን ፡ የበገናንና የዋሽንትን ፡ የዘፈንንም ሁሉ ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ፡ ተደፍታችሁ ንጉሡ ናቡከደነፆር ላቆመው ለወርቁ ምስል እንድትሰግዱ ታዝዛችኋል ፡ ተደፍቶም የማይሰግድ በዚያን ጊዜ በሚነድ እሳት እቶን ውስጥ ይጣላል ። ስለዚህ በዚያን የመለከቱንና የእንቢልታውን የመሰንቆውንና የክራሩን ፡ የበገናውንና የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ በሰሙ ጊዜ ፡ ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ተደፉ ፡ ንጉሡም ናቡከደነፆር ላቆመው ለወርቅ ምስል ሰገዱ ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚያን ጊዜም ከለዳውያን ቀርበው አይሁድን ከሰሱ። ለንጉሡም ለናቡከደነፆር ተናገሩ እንዲህም አሉ ፦ ንጉሥ ሆይ ፤ ሺህ ዓመት ንገሥ ። አንተ ፤ ንጉሥ ሆይ ፦ መለከትንና የእንቢልታን ፤ የመሰንቆንና የክራርን ፤ የበገናንና የዋሽንትን ፤ የዘፈንንም ሁሉ ድምፅ የሚሰማ ሰው ሁሉ ተደፍቶ ለወርቁ ምስል ይስገድ ፤ ተደፍቶም የማይሰግድ በሚነድ እሳት እቶን ውስጥ ይጣላል ብለህ አዘዝህ ። በባቢሎን አውራጃ ሥራ ላይ የሾምሃቸው ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም የሚባሉ አይሁድ አሉ ፤ ንጉሥ ሆይ ፤ እነዚህ ሰዎች ትእዛዝህን እንቢ ብለዋል ፤ አማልክትህን አያመልኩም ፤ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል አይሰግዱም ።

ናቡከደነፆርም በብስጭትና በቁጣ ሲድራቅንና ሚሳቅን አብደናጎንም ያመጡ ዘንድ አዘዘ ፤ እነዚህንም ሰዎች ወደንጉሡ ፊት አመጡአቸው ። ናቡከደነፆርም ፦ ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም ሆይ ፤ አምላኬን አለማምለካችሁ፤ ላቆምሁትም ለወርቁ ምስል አለመስገዳችሁ እውነት ነውን አሁንም የመለከቱንና የእንቢልታውን የመሰንቆውንና የክራሩን የበገናውንና የዋሽንቱን የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ተደፍታችሁ ላሠራሁት ምስል ብትሰግዱ መልካም ነው ፤ ባትሰግዱ ግን በዚያ ጊዜ በሚነድድ እሳት እቶን ውስጥ ትጣላላችሁ ፤ ከእጄስ የሚያድናችሁ አምላክ ማን ነው ? ብሎ ተናገራቸው ። ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም መለሱ ንጉሡንም ፦«ናቡከደነፆር ሆይ ፤ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም ። የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል ፤ ከእጅህም ያድነናል ፤ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን ፤ እርሱ ባያድነን ፤ አማልክትህን እንደማናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንደማንሰግድለት እወቅ አሉት ።

የዚያን ጊዜም ናቡከደነፆር በሲድራቅና በሚሳቅ በአብደናጎም ላይ ቁጣ ሞላበት፤የፊቱም መልክ ተለወጠባቸው ፤ እርሱም ተናገረ ፤የእቶንም እሳት ይነድ ከነበረው ይልቅ ከፍ እንዲል አዘዘ። ሲድራቅንና ሚሳቅንም አብደናጎንም ያስሩ ዘንድ፤ወደሚነድድም ወደ እቶን እሳት ይጥሉአቸው ዘንድ በሠራዊቱ ውስጥ ለነበሩት ኃያላን ትእዛዝ ሰጠ ። የዚያን ጊዜም እነዚህ ሰዎች ከሰናፊላቸውና ከቀሚሳቸው ከመጐናጸፊያቸውም ከቀረውም ልብሳቸው ጋር ታስረው በሚነድድ በእቶን እሳት ውስጥ ተጣሉ ። የንጉሡም ትእዛዝ አስቸኳይ ስለሆነ የእቶኑም እሳት እጅግ ስለሚነድድ፤ ሲድራቅንና ሚሳቅን አብድናጎንም የጣሉአቸውን ሰዎች የእሳቱ ወላፈን ገደላቸው ። እነዚህም ሦስቱ ሰዎች ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም ታስረው በሚነድደው በእቶን እሳት ውስጥ ወደቁ ።

የዚያን ጊዜም ንጉሡ ናቡከደነጾር ተደነቀ ፤ፈጥኖም ተነሣ ፤ አማካሪዎቹንም ፦ሦስት ሰዎች አስረን በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረምን ? ብሎ ተናገራቸው ። እነርሱም፦ ንጉሥ ሆይ ፤ እውነት ነው ብለው ለንጉሡ መለሱለት ።



www.ethiopianorthodox.org

እርሱም ፡— እነሆ ፤ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚ መላለሱ አራት ሰዎችን አያለሁ፤ምንም አላቆሰላቸውም ፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል ብሎ መለሰ ። የዚያን ጊዜም ናቡከደነፆር ወደሚነድደው ወደ እሳቱ እቶን በር ቀርቦ ፡— እናንተ የልዑል አምላክ ባሪያ ዎች ፤ ሲድራቅና ሚሳቅ አብድናጎም ፡ ኑ ውጡ ብሎ ተና ገራቸው ። ሲድራቅና ሚሳቅም አብደናጎም ከእሳቱ መካ ከል ወጡ ። መሳፍንቱና ሹማምንቶቹም አዛገሮቹና የን ጉሡ አማካሪዎች ተሰብስበው እሳቱ በእነዚያ ሰዎች አካል ላይ ኃይል እንዳልነበረው ፤ የራሳቸውም ጠጉር እንዳልተ ቃጠለች ፤ ሰናፊላቸውም እንዳልተለወጠ ፤ የእሳቱም ሽታ እንዳልደረሰባቸው አዩ ።

ናቡከደነፆርም መልሶ፡— መልአኩን የላከ ፤ ከአም ላካቸውም በቀር ማንንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የንጉ ሡንም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን ያዳነ ፤ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብድናጎም አምላክ ይባረክ። እኔም እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና በሲድራ ቅና በሚሳቅ በአብድናጎም አምላክ ላይ የስድብን ነገር የሚናገር ወገንና ሕዝብ በልዩ ልዩም ቋንቋ የሚናገሩ ይቆ ረጣሉ ፤ ቤቶቻቸውም የጉድፍ መጣያ ይደረጋሉ ብዬ አዝዣለሁ»አለ ። የዚያን ጊዜም ንጉሡ ሲድራቅንና ሚሳ ቅን አብደናጎንም በባቢሎን አውራጃ ውስጥ ከፍ ከፍ አድርጎ ሾማቸው » ።




www.ethiopianorthodox.org

በቅድሚያ የታሪኩን መነሻ በትንቢተ ኤርምያስ ምዕ ፡ ፳፪ ፡ ፲—፲፱ እንመልከት ።

አናንያ አዛርያና ሚሳኤል ተብለው የሚጠሩት ሠለስቱ ደቂቅ ትውልዳቸው ከይሁዳ ቤተ መንግሥት ወገን ሲሆን አባታቸውም ንጉሥ ኢዮአቄም ይባል ነበር ። ይህም ኢዮአቄም በእግዚአብሔር ፊት የሠራው በደል ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ነቢዩ ኤርሚያስ በርሱ ላይ የተናገረበት አስፈሪ የትንቢት ቃል እንዲህ የሚል ነበር ።«ኢዮአቄም በዚህች ምድር የመቃብር ቦታ እንኳ የማግኘት ዕድል ፈንታ አይኖረውም ፡ ስለዚህም ? መቃብሩ እንደ አህያ የጅብ ሆድ ይሆናል ። ምክንያቱም ሬሣው ከኢየሩሳሌም ቅጽር በር ወደ ውጭ ተጐትቶ ይጣላል»(ኤር፡ ፳፪ ፥ ፲—፲፱

ስለዚህም ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን በወረሩ ጊዜ አገሪቱ ጉዳት ላይ ወድቃ ወደባቢሎን ለመሰደድ ጉዞው እንደ ተጀመረ ኢዮአቄም በመንገድ ስለሞተ በትንቢቱ መሠረት ጅብ በልቶት የትም ቀርቷል ።

ልጆቹም ሐናንያ አዛርያና ሚሣኤል ይህን አሳዛኝ ድርጊት ያውቁ ስለ ነበር አባታቸው ይፈጽመው የነረበውን የበደል ሥራ መድገም አልፈለጉም።ከዚህም የተነሣ ሌላው ቀርቶ በስደት በሚኖሩበት ምድረ ባቢሎን ተመርጠው በንጉሥ ናቡከደነፆር ቤተመንግሥት የከለዳውያንን ቋንቋ እየተማሩ እንዲያድጉ ተፈቅዶላቸው ስለነበር በዚያ በቤተ መንግሥት ት/ቤት ለሚማሩ ሁሉ ንጉሡ ከሚበ

ሳው ከሚጠጣው ከማለፊያው ምግብ እንዲሰጣቸው ታገዞላቸው ሳለ እነርሱ «ዓለማዊ ተድላ ደስታስ እርም ይሆንብን»ብለው ከነቢዩ ዳንኤል ጋር በመተባበር ሽንብራ እየቆረጠሙ ውሀ እየጠጡ ይማሩ ነበር ። እግዚአብሔርም በረድኤት ስላልተለያቸው ማለፊያ ምግብ ይበሉ ከነበሩ ከጓደኞቻቸው ይልቅ የነርሱ ፊት በጸጋ እግዚአብሔር እንደ ፀሐይ ያበራ ነበር ።

ስማቸው ተለውጦ ሲድራቅ ሚሳቅ አብደናጎ የሚል ባቢሎናዊ ስያሜ ተሰጥቶአቸው ነበር ፤ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት ግን እስከ መጨረሻይቱ ሕቅታ አልተለወጠም ።

በዚህም ተጠቀሙበት እንጂ አልተጐዱበትም፤ ተሾሙበት እንጂ አልተሻሩበትም ።

እንግዲህ የፍጹም ታማኝነት አሠራር የመጨረሻ ውጤቱ እስከዚህ ድረስ ስለሆነ ይህ ዓይነቱ መንፈሰ ጠንካራነትና የሃይማኖት ጥበዓት በዘመናችንም ሆነ ወደፊትም ጭምር በያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሠርጾ እንዲኖር ያስፈልጋል ። ዕውነተኛ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ጽኑዕ እምነትና እውነተኛ ምስክርነቱ ለዘላለም የማይናወጥና ለቆለመላት ዓላማ ታማኝ ሆኖ የመገኘት ጠባዩ ከደሙ ጋር ተዋሕዶት እንዲኖር ያስፈልጋል ።

ይህ ከሆነ ዛሬም ቢሆን እንደ ሠለስቱ ደቂቅ ለቆሙለት እምነት እስከመጨረሻው ጸንተው የሚገኙ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖች ቢኖሩ የዚህም ዓለም ተድላ ደስታ ሳይ ቀርባቸው ሰማያዊት በሆነችው በእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ መቶ ዕጥፍ ዋጋ፡ዕፅፍ ድርብ ክብር የሚጠብቃቸው መሆኑ ተጽፎአል (ማቴ ፲፱ ፡ ፳፯—፴/ ።

ታዲያ እኛ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛገ'ችና ታማኞች አገልጋዮችም መሆን የሚገባን እርሱ ለእኛ መልካም ነገር አድርጎልን በተመቸን ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ወይም ነብዩ ሆሴዕ «በምንዳቤሆሙ ይገይሱ ኀቤየ በችግራቸው ጊዜ ብቻ ወደ እኔ ይሮጣሰ. ሲል እንደ ተናገረ ዳዊትም የአምነክ ሰብእ ሰቦ ታሤኒ ሎቱ አንተ መልካም ነገር ባደረግህለት ጊዜ ሰው ሁሉ ያምንሃል ሲል እንደመሰከረ እርሱ ለእኛ መልካም ቸርነትን ባደረገልን ጊዜ ብቻ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ እያልን የትንሽ ፈተና ወላፈን በምትገርፈን ጊዜ ሽርተት ማለት አደገባም ።

በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት የተመሠረተው «ይህን ቢያደርግልን ይህን እናደርግለታለን እንዲህ ብለን እንዘምርለታለን በሚል የውለታ ድርድር አይደለም ።

ምንም ዓይነት ይሁን ፈተና በገጠመን ጊዜ እንደ አናንያ አዛርያና ሚሳኤል ለዓለማችን ጸንተን እንድንቆም ይፈለግብናል ። የመንፈስ ጽንዓትና የእምነት ኃይል ሊኖረን ይገባል ።

እነዚህ ሦስቱ ወጣቶች በድፍረት ሲናገሩ «እግዚአብሔር ሊያድነን ባይፈቅድ እንኳ ለዚህ ሰው ሠራሽ የወርቅ ምስል



www.ethiopianorthodox.org

እንደማንሰግድለት ዕወቅ» ሲሉ የተናገሩትን ያን ቍርጠኛ ቃል ደግመን ደጋግመን ልንናገረው ይገባል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ምዕ ፲፩ ፡ ስለ ሃይማኖት ሰዎች ተጋድሎ ሲያወሳ «እነርሱ በእምነት ነገሥታትን ድል ነሡ ፡ ጽድቅን አደረጉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ የአንበሶችን አፍ ዘጉ የእሳትን ኃይል አጠፉ ፡ ከሰይፍ ስለት አመለጡ ከድካማቸው በረቱ» በማለት የሃይማኖትን ኃይል ያስረዳል

በሮሜ መልእክቱም ይኸው ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው የሐዲስ ኪዳን ፍካሬ « እሱ ወዶናልና ስለዚህ በርሱ ሁሉን ድል እንነሳለን» የሚል ነው ።

እንግዲህ ይህን ዓይነት ቍርጥ ውሣኔ አድርገን በፍጹም እምነት ለዕእውነተኛ ምስክርነትና ዓላማ እስከሞት ድረስ ጸንተን ስንቆም ብቻ ነው እግዚአብሔር አምላክ ከእኛ ጐን የሚቆሙና ሊታደጉን የሚችሉ መላእክቱን የሚልክልን ። ይህም ዓይነት ሃይማኖታዊ ውሳኔ ካለን «እናንተ የራስ ጠጉራችሁእንኳ የተቈጠረ ስለሆነ አትፍሩ» ተብሎ በወንጌል የተጻፈ ቃሉ የታመነ መሆኑ ብዙ ጊዜ በተግባር ታይቷል ።

ቀድሞ ለአባቶቻችን ይሠራው የነበረው ድንቅ ነገር ሁሉ በዘመናችንም ዘወትር እየተደገመ ነው፤ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር በዚህ ቅ/መልአክ ገብርኤል አማላጅነት የሚያሳየው ገቢረ ተአምር በዕጥፍ እየጨመረ መምጣቱን እናያለን ።

በተለይም በስሙ በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሥዕለትና ብፅዓት በየጊዜው ተፈጻሚነት እያገኘ በመላው ዓለም እንኳን ሃይማኖት ያላቸው ሃይማኖት የሌላቸውም ስሙ በተጠራበት ቦታ እየተገኙ የእግዚአብሔርን ቸርነት የመላኩን አማላጅነት እየመሰከሩ ናቸው ።

አሁንም በእምነት ጸንተን በምንቆም መጠን ለችግራችን ሁሉ የሚረዳንን ይህን ተራዳኢ መልአክ የፈጠረ ያከበረ የአናንያ የአዛርያና የሚሳኤል አምላክ ቅዱስ ስሙ ተመስገን ይሁን ፤

ያደረጋችሁት ሥዕለት ብፅዓት ተሰምቶላችሁ የፈ ድኤት መልስ ያገኛችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ! የቍጥራችሁ ብዛት ዕልፍ አዕላፍ የሆነ እናንተ ቅዱሳን የሰ ማይ መላእክትም የምሕረት የሰላምና የፍቅር አንድነት ባለቤት የሆነ ጌታን ለምኑልን፤እናንተም ምእመናን በርሱ ላይ ያላችሁ የማይናወጥ እምነት እስከ መጨረሻው ይጽና ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ።

አሜን ።

## ለሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል የተሰጠው ሀብተ ብሥራት

ታሪኩ ባጭሩ እንዲህ የሚል ነው ። «መልአኩ ቅ/ገብርኤል ቀደም ሲል ልደተ ዮሐንስን ለዘካርያስ ባበሠረ በስድስተኛው ወር በገሊላ አውራጃ ናዝሬት ተብላ ወደምትጠራው ከተማ ከእግዚአብሔር ተልኮ ሔደ፤ማርያም ተብላ የምትጠራውም ንጽሕት ቅድስት ድንግል ወደ አለችበት ገብቶ በመጀመሪያ ሰላምታ ካቀረበላት በኋላ ! « ጸጋን የተመላሽ ድንግል ሆይ!አንቺ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነጽሕት ክብርት ነሽ ። ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን ሞገስን አግኝተሻልና አትፍሪ ! እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ፤እርሱ ታላቅ ነው እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ፤ በቤተ ያዕቆብም ለዘለዓለም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም ፤ ይህም እንዲፈጸም መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፣የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ፤ ስለዚህም ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው ። የልዑል እግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

ልጅ ይባላል ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና » ሲል አበሠራት ። ሉቃስ ፩ ፡ ፳፮—፴፰ ።

ከዚህ አስቀድሞ በነቢዩ ኢሳይያስ«ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል፣እነሆ ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች» ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሞ መድኀነ ዓለም ክርስቶስ በቤተ ልሔም በተወለደበት ዕለት ይኸው ቅ/ገብርኤል ከሌሎች ሠራዊተ መላእክት ጋር ተገልጦ ለቤተ ልሔም እረኞች ለዓለም ሁሉ የሚሆን ዘለዓለማዊ ደስታን የሚሰጥ መድኅን የመወለዱን የምሥራች ነገረ ። /ሉቃ ፪/ ፲—፲፪/

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ዕርቀ ሰላም የተወጠነበት መሆኑን በመግለጽ የሰማይ ሠራዊት ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ» እያሉ የዘመሩት ቃል በሉቃስ ፪ ፡ ፲፬ ተጽፎ ይገኛል ።

«ዘያፈትዎሙ ለመላእክት ከመ የሐውጽዎ»እንዲል መላእክት እንዲመኙትና «ሥግው ሆኖ የማዳኑን ኃይል ምን ጊዜ አይተነው? እያሉ በናፍቆት እንዲጠብቁ ያደረጋቸውም ይኸው ነበር፣ ጴጥ ፩ ፡ ፲፪ ።



መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ መዳን በእግዚአብሔር መላእክት ዘንድ እልልታና ደስታ ይሆናል ። /እብለክሙ ከመ ይከውን ፍሥሐ በሰማያት በቅድመ መላእክተ እግዚአብሔር በእንተ አሐዱ ኃጥእ ዘይኔስሕ» ይላል /ሉቃ ፲፭ ፡፲/ «መላእክት ወሰብእ ዮም አሐደ መርኤት ኮኑ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ» ተብሎ እንደተጻፈ በክርስቶስ ልደት ሰውና መላእክት በአንድነት የዘመሩትም ቃል «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረት ለሰብእ በሰማያት ለሚኖር ለእግዚአብሔር ምስጋና ይ ባል ፤ ሰላም በምድር ፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ» የሚል ሲሆን በሰው ዘር ደህንነት መላእክተ እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅ ደስታ እንዳላቸው ያመለክታል ።

ዳዊት በመዝሙሩ «ይትአየን መልአከ እግዚአብሔር ዓውደሙ ለእለ ይፈርህዎ ወያድኅኖሙ የእግዚአብሔር መላአከ እግዚአብሔርን በሚፈሩት በሚያመልኩት ሰዎች ዙሪያ ይከታተማል ከመከራም ያድናቸዋል»ሲል እንደተና ገረ ለዕውነተኛ ምስክርነት የሚቆሙ አማኞችን ከጥፋት ሁሉ ለመታደግ የሚችሉ ቅዱሳን መላእክትን በመላክ ድንቅ ሥራውን ለዘለዓለም ሳያቋርጥበት የምንኖርበት ይህን የጸጋ ዘመን በልደቱ ያድሰልን አምላክ ይመስገን ፡

አሜን ፡



www.ethiopianorthodox.org



ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ



## ሕፃኑ ሰማዕትና የተላከለት ታዳጊ መልአክ

«ጥብአ.ኪ እም ወኢ.ትናፍቂ እናቴ ሆይ አይዞሽ በርቺ ያለምንም መጠራጠርና ያለፍርሃት ይህን ፈተና ለማለፍ ጨክነሽ ክርስቶስን በማመን ለቆምሽለት ዓላማ እውነተኛ ምስክር መሆን ይገባሻል»በማለት ይህን የማበረታቻ ቃል የተናገረው ሕፃኑ ሰማዕት ቅ/ ቂርቆስ ነው፡ይህንም በተናገረበት ጊዜ ዕድሜው ከሦስት ዓመት የሚበልጥ አልነበረም ። ታዲያ ይህን አበረታች ቃል እንዴት መናገር ቻለ? ብለን ብንጠይቅ በርሱ አድሮ ባለው በመንፈስቅዱስኃይል መሆኑን እንገነዘባለን ።

ከዚህም የተነሣ ፤

«ነገረ ቃልከ ያበርህ ወያጠብብ ሕፃናተ የቃልህ ንግግር አዕይንተ አእምሮን ያበራል፡ሕፃናትንም ጥበበኞችና አስተዋዮች ያደርጋል» ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔር እንኳንስ ግዕዛነ አእምሮ ያላቸውን ሕፃናት ይቅርና ዕድግተ በለዓምን ያናገረ ነውና «አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር ለርሱ የሚሳነው ነገር የለም» ብለን ከማድነቅ በቀር ሌላ መልስ አይኖረንም ።



www.ethiopianorthodox.org

የቂርቆስ እናቱ ቅ/ኢየሉጣ አማኝ ስለ ነበረች አንድ ሮማዊ መስፍን ሀገር ያሳድዳት ነበር፡ከሮም ተሰዳ በሄደች በትም አገር ያንኑ መስፍን አገኘችውና እንደገና በይበልጥ መከራ አጸናባት ። ካጸናባትም ጽዋትወ መከራ አንዱ በሕፃኑ ልጅዋ ቂርቆስ ላይ የተቃጣው ሰይፍ ነበር ።

በእርሱ ላይ ልዩ ልዩ ማስፈራሪያ በማሳየት ሃይማኖቷን እንድትክድ ለጣዖትም እንድትሰግድ በጠየቃት ጊዜ »ወወሀቦ እግዚአብሔር ኃይለ ወጥብበ፡እግዚአብሔር ኃይልና ጥበብን ስለሰጠው የሦስት ዓመት ልጅ ሕፃኑ ቂርቆስ ያንን መኰንን መስፍን ሀገርና ጣዖታቱን ሁሉ እየረገመ ስላስቸገረው በብረት ጋን ውሃ አስፈልቶ ሲግል ሕፃኑን ቂርቆስንና እናቱን ቅ/ኢየሉጣን ለመቅጣት ወሰነ ሕፃኑ ቂርቆስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመልቶ ከናቱ ጋር ወደዚያ ንፍር ውሃ ጋን ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ፡እግዚአብሔርም ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ በመልአኩ እጅ ታደጋቸው፡እሳቱን አጠፋላቸው ውሀውንም አበረደላቸው ከመከራው አዳናቸው፤ «አህለፍከነ ማእከለ እሳት ወማይ ወአውዳእከነ ውስተ ዕረፍት በእሳትና በውሃ መሀ



ከል አሳለፍከን ወደ እረፍትም አወጣህን» ብለው ለመመ
ከርና ለማመስገን አበቃቸው ።

አረማውያን አማኞችን ለመጉዳት በማሰብ ሆን ብለው ይ
ጽሙትከነበረው ጭካኔ አንዱ በወላጆቻቸው ፊት አቅርበ
ምንም የማያውቁ ሕፃናት ልጆቻቸውን ዓይናቸው እያ
በሰይፍ መቅጣት ወይም በእሳት በስለት እያስፈራሩ ል
ቸውን ለማበሸር ሃይማኖታቸውን በማስካድ ለጣዖ
መስገድ የተለመደ ሥርዓታቸው ነበር ። በቅድስ
ኢየሉጣና በሕጻኑ ልጅዋ ቂርቆስ ላይ የተፈጸመው
ግፍ ከዚህ የተለየ አልነበረም ።

ነገር ግን በዕውነተኞች አማኞች ዘንድ የሞት ቅጣ
ምንድነች? ሐዋርያው ጳውሎስ«በዚህ ዓለም ማለን ሊደ
ስብን የሚችል ማንኛውም ዓይነት መከራ ከሞት በኋ
ከምናገኘው ዘለዓለማዊ ክብር ጋር ሲነፃፀር ሕማሙ ለዘ
ዓለም የዚህ ዓለም መከራ ከምንም ሊቆጠር የማይችል
ኢምንት ነው» ይለዋል ። ስለምን? ቢባል«ነአምር ከ
ሕማም ይፌጽም ትዕግሥተ ላዕሌነ ወትዕግሥት መከ
ወበመከራ ይትረከብ ተስፋ ወተስፋኒ ኢያስተ ኃፍር»ሮማ



www.ethiopianorthodox.org

፫—፬ የመከራ ጽናት የትዕግሥትን ምንነት እንደሚያስተ ምረን የትዕግሥትም ብዛት መከራን እንደሚያለማምደን እናውቃለን ፤ መከራ በመቀበልም የምናገኘው ፍጹም ተስፋ አለን ያም ተስፋ የማያሳፍር ነው»ሲል እንደተና ገረው እንዲያውም«ምነው በመከራ ላይ መከራን በተቀበ ልኩበት ? ያሰኛል እንጂ ያን ያህል የተፈተንኩት ለዚህ ነበር እንዴ ? » በማለት የሚያስጸጽት አይደለም ።

መፍቀሬ ሃይማኖት ቆስጠንጢኖስ ብፁዓን መነኮሳት በአክናፈ እሳት ወደሰማያዊት ኢየሩሳሌም በክብር ሲያርጉ አይቶ አባ ብሰይ ተብሎ የሚጠራውን መነኩሴ «ሰላም ለክሙ አብፁዓን መነኮሳት» ቢለው«አንተም እንጂ ንዑድ ክቡር ነህ ምክንያቱም በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቆሟል» አለው።ቆስጠንጢኖስም መለስ አድርጎ«የመነኮሳት ክብራ ቸው እንዲህ መሆኑን አውቄ ቢሆን ኖሮ መንግሥቴን ለቅቄ፡ ዳባ ታጥቄ፡ዳዋ ጥሼ፡ጤዛ ልሼ፡ደንጊያ ተንተርሼ በምናኔ በኖርሁ ነበር » ብሎታል ።

ይህም ዕርግጥ ነው በክርስቶስ የተሰጠን ተስፋ የሚያ ሳፍርና የሚያስፀፅት ባለመሆኑ ሁላችን ይፀ ዓይነቱ የሃ ይማኖት ጥብአት ያስፈልገናል።የሕፃኑ ቂርቆስንና የእናቱ



የቅ/ ኢየሉጣን አሠረ ሃይማኖት ብንከተል «ተስፋው ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ለሚ ጠራቸው በሩቅ ላሉትም ሁሉ የተሰጠነው» ተብሎ ተጽ ፎአል። ስለዚህ በዚህ ዘለዓለማዊ ተስፋ ደስ ይበላችሁ ኢትፍርህዎሙኬ ለእለ ይቀትሉ ሥጋክሙ ወለነፍሰ ክሙሰ ኢይክሉ ቀቲሎታ ፡ ቢበዛ ሥጋችሁን እንጂ ነፍሳችሁን መግደል የማይቻላቸውን ተፈታተኞች አትፍሩ ወለዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ እነሂ አክሕዶ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት ። በሰው ፊት የሚክደኝን እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በቅዱሳን መላእክት ፊት እክደ ዋለሁ በሰው ፊት ቆሞ የሚመሰክርልኝን ግን እኔ ደግሞ በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ «ተብሎ በወንጌል የተጻ ፈውን ቃል በመጠበቅና በሥራ በመተርጐም ረገድ ሕፃኑ ቂርቆስና ቅድስት እናቱ ኢየሉጣ ጥሩ ምሳሌነታቸውን ትተውልን አልፈዋል ።

ጌታችንም በቅዱስ ወንጌል«ዑቁ ኢታስተሐቅርዎ ለ፩ዱሂ እም እሉ ንኡሳን እብለክሙ ከመ መላእክቲሆሙ በሰማያት ወትረ ይሬእዩ ገጾ ለአቡየ ዘበሰማያት ። ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ስንኳ እንዳታቃልሉ ተጠንቀቁ ጠባቂ



www.ethiopianorthodox.org

ዎቻቸው መላእክት ሁልጊዜ በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት እንዲያዩ እነግራችኋለሁ»ብሎአል።በዚህም መሠረት እግዚአብሔር አምላክ ቅዱስ ገብርኤልን በመላክ ሕፃኑንና እናቱን ከመከራ ታደጋቸው። ይህም ታዳጊነቱ ምን ጊዜም የማይገታ ስለሆነ በዘመናችንም በሥራ ላይ ነውና ክርስቲያን ሁሉ ተስፋ መቊረጥ አይገባውም ።

በማናቸውም ጸዋትወ መከራ ለሞት በሚያደርስ ፈተና እንኳን ልንፈታ አይገባምንም፤ክርስቲያን ይፈራ ዘንድ ሞት ራሱ ምንድን ነው?በምንም ዓይነት መልክ ተለዋውጦ ይምጣ ሞት ለክርስቲያኖች ከዚህ ዓለም ድካም ተለይተው የዘለዓለም ዕረፍት ወደሚያገኙባት ገነት መንግሥተ ሰማያት መሸጋገሪያ ድልድይ ነው ። ወይም ወደ ሰማያዊ አባታችን የምናርግበት መሰላል ነው ።

ፈተናም ቢሆን የእምነታችን ጽርየት እንደወርቅ ንጥሮ የሚወጣበት ስለሆነ ልንሰቀቀው የሚገባ አይደለም ስለዚህም እንደነ ቅ/ቂርቆስ ከፍርሃት የነጻ የእምነት ጥብአት ሊኖረን ይገባል «ፍርሃትሰ መቅሠፍት ባቲ ፍርሃት ራስዋ መቅሠፍት ናት» ሲል ዮሐንስ ወንጌላዊ በመጀመሪያ መላእክቱ እንደተናገረ ማንም ክርስቲያን የፍርሃት ተገዢ መሆን የለበትም ። ማንንም ሰው ስለፈራ ደግሞ ሞት ይቀርለታልማለት አይደለም።እንዲያውም ለሕይወቱ ሳስቶ ነፍሱን ለማትረፍ የሚስገበገብላት ሰው በማዳን ፈንታ ከነጭርሱ ያጠፋታል።ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ ይረክባ ሰውነቱን ስለ እኔ የጣላት ግን በኋለኛው ዘመን በትንሣኤ ሕይወት ያገኛታል» ሲል መድኅነ ዓለም አምላካችን ክርስቶስ የተናገረው ቃለ ወንጌል ምን ጊዜም የማይታበል ነው ።

በእምነት የሚያወላውሉ በዚህ ዓለም ኑሮ እንኳ ሳይ ሳካላቸው በመቅረቱ ባለቅኔው ።

« ተረፍነሂ እለ ተረፍነ በውስተ ዓለማት ክልኤቲ እንዘ ለዛቲ ኢንከውን ወእንዘ ኢንከውን ለእንታክቲ፤ከሁለቱ ዓለማት ማለትም ከሥጋዊውም ሆነ ከመንፈሳዊው ዓለማት አንዱን ሳንይዝ በመካከል ተንገዋለን ቀረን?» እንዳሉት በወላዋይነት ተንሳፈው የቀሩም ብዙ ናቸው ።





www.ethiopianorthodox.org

ዓላማ ቢስ ሆኖ በሕይወት ታሪክ ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ከማለፍ ይልቅ እንደ ሕፃኑ ቂርቆስና ቅ/ኢየሉጣ ተፈላጊውን የሕይወት መሥዋዕትነት ከፍሎ የክብር አሟሟትን ማሳመር የእውነተኛ ክርስቲያን ዘላቂ ዓላማ ነው ። ይህም ዓይነቱ የሃይማኖት ጥብአት ካለን ደግሞ እስከ መጨረሻው እንጠፋ ዘንድ የሕያው አምላካችን ፈቃድ አይደለም ፤ እርሱ ወዳጆቹን ያውቃል፤ ከዚህም የተነሣ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ፈተና እንዲደርስባቸው አይፈቅድም። ሐዋርያው ጳውሎስ ይረድአክሙ በመከራ ከመ ትጻኡ እመንሱት፣ በመከራ ጊዜ ከፈተና የምትወጡበትን መንገድ ያዘጋጅላችኋል» ሲል የተናገረው የተስፋ ቃል በዕርግጥ የታመነ ነው ። (፩ ቆሮ ፲ ፡ ፲፫ ) ።

በዕርግጥም ይላል ሐዋርያው በዕብራውያን መልእክቱ ምዕ ፮ ፡ ፲፰—፲፱ ፡«ዐቢይ ፍሥሐ ብነ ለእለ ተማሕጸነ ወአጽናዕነ ተወክሎ በስተፋነ ዘጽኑሕ ለነ እንተ ታጸንዓ ከመ መርሶ ለነፍስነ ከመ ኢታንቀልቅል ፡ ሃይማኖታችንን አጽንተን ይዘን ለምንገኝ ለእኛ ፍጹም ተስፋ አለን ይህም ተስፋ ለሕይወታችን እንደማይነቃነቅ አስተማማኝ መልኅቅ ነው ።



በዚህም አስተማማኝ ተስፋ መሠረትነት ሰማዕትን በደም ፤ ጻድቃንን በገዳም ያጸና ሕያው አምላካች ከሰማዕቱ ሕፃን ቂርቆስና ከቅድስት እናቱ ኢየሉጣ ረ ኤትና በረከትን ያሳድርብን፣ የሊቀ መላእክት ቅ/ገብርኤንም ተራዳኢነት ሳያርቅብን ሀገራችንንና ሕዝባች በሰላም ይጠብቅልን ለዘለዓለሙ ።

አሜን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ማስታወሻ

—ይህ አጭር ጽሑፍ ለኅትመት የበቃው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ በሰጡት መመሪያና የሞራል ድጋፍ ፤

—እንዲሁም በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ትብብር ነው ።

www.ethiopianorthodox.org